# የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ በሸካቾ ብሔረሰብ*

(ግሩም አረዳ†፣ ዓለሙ ካሣዬ‡ እና የኔዓለም አረዶ§)

**አጠቃሎ:** የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔን መተንተን ነው። ጥናቱ በሸካቾ ዞን አንድራቻ እና ማሻ ወረዳዎች በሚገኙ ስምንት ቀበሌዎች ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ ዓይነታዊ ገላጭ (Qualitative Descriptive) የምርምር ስልትን የተከተለ ሲሆን ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርጓል። የተሰበሰቡ መረጃዎችን ትርጉም ለመፈከር የክዋኔ መርና የትዕምርት ንድፈ ሀሳቦች ጥቅም ላይ ውለዋል። በጥናቱም የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የተፈጸመበት መቼት፣ የክዋኔውን ሂደት፣ የከዋኞቹን የአከዋወን ስልት፣ ክዋኔውን ይመለከቱ የነበሩ ተሳታፊዎች ለክዋኔው የነበራቸውን ስሜት እንዲሁም የድርጊቶችና የቁሶች ውክልና ተተንትነዋል። የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ የሚቀርብ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ነው። የሸካቾ አባወራ ካመረተው ምርት ላይ ምንም ሳይነካ፣ ለቤት ፍጆታ ቀድሞ ሳያውል፣ ሳይሸጥና ሳይለውጥ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መስዋዕት ያቀርባል። በምላሹ ደግሞ የአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ የተመረተውን ምርትና ህይወታቸውን እንደሚባርክ፣ ከፈጣሪ (ከየሮቺ) ጋር እንደሚያስታርቅ፣ በራዕይ ወይም በመንፈስ ተገልጦ ምድራዊ ቤተሰቦቹን እንደሚመክርና እና እንደሚገስጽ፣ የሚያጋጥሟቸውን የህይወት ውጣ ውረዶች እና ውጥረቶች መቋቋም እንዲችሉ ያግዛል ተብሎ በብሔረሰቡ ዘንድ እንደሚታመን በጥናቱ ተመላክቷል።

***ቁልፍ ቃላት፤*** *ሸንበተ ቆጮ፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ መንጻት፣ መስዋዕት፣ ክዋኔ፣ ትዕምርት*

---

* ይህ ርዕስ "የጉዶ ኬሶ እና የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነቶች ክዋኔ በሸካቾ ብሔረሰብ" በሚል ለሦስተኛ ዲግሪ እየተደረገ ካለው የማሟያ ጥናት፣ አንደኛውን ንዑስ ዓላማ በመውሰድ ለዚህ ጽሑፍ በሚመጥን መልኩ የቀረበ ነው፡፡

† በፎክሎር የፒ.ኤች.ዲ ተማሪ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ girumee@gmail.com

‡ የፎክሎር መምህር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ alemukas@gmail.com

§ የፎክሎር መምህር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ yenealem2006@yahoo.com

## መግቢያ (የጥናቱ ዳራ)

ሸንበተ ቆጮ (Shenbete Kochoo) የአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ ክዋኔ፤ የሸካቾ አባወራ ትኩረት ሰጥቶ በየዓመቱ በቤት ውስጥ ከሚከውናቸው ክዋኔዎች መካከል ይጠቀሳል፤ አባወራው ያመረተውን ምርት ምንም ሳይነካ፣ ለቤት ውስጥ ፍጆታም ሆነ ለገበያ ሳያቀርብ ከምርቱ ላይ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መስዋዕት ያቀርባል[1]። የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማም ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ የሚደረገውን 'የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ መተንተን' ነው። ይህን ዓብይ ዓላማ ለማሳካት፣ የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ስርዓተ ክዋኔ ሂደት ምን ይመስላል? ሸንበተ ቆጮ በመከወኑ የሚገኘው ጥቅምና ባይከወን ሊደርስ የሚችለው ጉዳት እንዴት ይገለጻል? በክዋኔዎቹ ውስጥ የሚቀርቡ ቴክስቶች[2] ትዕምርታዊ ውክልናቸውና ፍቺያቸው ምንድን ነው? ለሚሉ መሪ የምርምር ጥያቄዎች ጥናቱ መልስ ሰጥቷል።

የሸንበተ ቆጮን ዳራ ከመዳሰሳችን በፊት 'እምነት' የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በቀዳሚነት ለማየት እንሞክር፤ እምነት (Belief) የሚለው ቃል በመንፈሳዊ (sacred) እና ዓለማዊ (secular) እይታው የተለያዩ ፍቺዎችና ብያኔዎች ያሉት ቢሆንም ጥናቱ ጽንሰ ሀሳቡን ከመንፈሳዊና ማህበራዊ ሳይንስ አቅጣጫው ብቻ ተመልክቶታል። Bell የእምነትን ጽንሰ ሀሳብን፤ "እምነት ሰፋ ያለ ጽንሰ ሀሳባዊ ግንዛቤ ያለው፤ በልማድ የምናገኘው፣ ግላዊና ቡድናዊ አስተሳሰቦች ያሉት፣ በልቦና አመክንዮ (Psycho Reasoning) የምንረዳው ነው (1997: 182)" በማለት ገልጸውታል። እንደ Sims እና Stephens (2005: 56) ደግሞ እምነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ፣ የሰዎችን ልቦናዊ ውቅርና እምነቱን የተመለከቱ ሌሎች ድርጊቶችን የሚያካትት ነው። እነዚህ ድርጊቶች፤ መለመንን፣ መማጠንን፣ መስገደን፣ አምልኮ መፈጸምን፣ መስዋዕት ማቅረብን ይጨምራሉ። በማለት እምነትን ከመንፈሳዊ እይታው አንጻር ተመልክተውታል።

በአጠቃላይ እምነት ማለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ የሚያራምዱት፣ ልቦናዊ አመክንዮ ላስቀመጡለት ነገር የሚታመኑበት፤ በጎ የሚሉትን ነገር እንዲፈፀምላቸው የሚጠይቁበት፣ ጻላኢ የሆነው ነገር ደግሞ እንዳይከሰትባቸው መስዋዕት በማቅረብ የሚለማመኑበት ሥርዓት ነው።

እምነት በፎክሎር ጥናት ውስጥ በሀገረሰባዊ ልማድ (social folk custom) ምድብ ስር ሀገረሰባዊ እምነት (Folk Belief) ተብሎ እንደሚጠና ፈቃደ (1991: 13) ይገልጻሉ። እንደ ፈቃደ ገለጻ፤

የሀገረሰባዊ እምነቶች ጥናት፤ በልዩ ልዩ በዓላት ላይ፣ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በሃይማኖት (መስጊድ፣ ቤተክርስቲያን፣ ምኩራብ ወዘተ) የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፤ በልደት፣ በግርዘት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን (interactions) ያካትታል፤ የጥናቱ ልዩ ትኩረት ግን ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ሀገረሰባዊ እምነቶችን እመመርመር ላይ ነው (1991: 14)።

---

[1] ቃ.መ አበራ በጭሮ፣ 10/04/2014 ዓ.ም)፣ (ቡ.ው) ፤(ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዘለቀ ሻጫቸው 29/08/14 ዓ.ም)

[2] ክዋኔው በሚቀርብበት ወቅት በንግግር እና በድርጊት የሚገለጹ እንዲሁም ግልጋሎት ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎችን ያጠቃልላል፡፡

በገለጻው መሰረት ሀገረሰባዊ እምነት የአንድ ሀገረሰባዊ እምነት ተከታይ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚተገብራቸው እምነታዊ ድርጊቶችንና ክዋኔዎችን የሚመለከት ሲሆን የጥናት ትኩረቱም እነዚህን ክዋኔዎች ከተለያዩ ጉዳዮች አኳያ የሚመረምር ነው።

ወደ ጥናቱ ጉዳይ ስንመለስ፤ የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ሁሉም የሸካቾ ጎሳዎች ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በቤት ውስጥ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መስዋዕት በማቅረብ የሚከውኑት ነው። ክዋኔው የሸካቾ ጎሳዎች ባሳለፏቸው የህይወት ውጣ ውረዶችና አጋጣሚዎች ውስጥ የጎሳ አባላቱን በእምነት አባትነታቸው የመሩ፣ ፈጣሪ ከከለከላቸው ነገሮች ታቅበው፣ ጎሳቸውን በመንፈሳዊ ህይወት ያነጹ፣ እምነታዊ ህግጋትን የፈጸሙ እና በጎሳ አባላት ዘንድ ከፍ ያለ እምነት የሚጣልባቸው ሰዎች ምድራዊ ኑሯቸውን ፈጽመው ከዚህ ዓለም ሲያልፉ ፤ ነፍሳቸው ወደ ፈጣሪ ያቀናል፤ በዚህ ጊዜ የጎሳ አባላቱ እንደ ቅዱስ ይቆጥሯቸዋል፤ አማልክት አድርጎ ይመለከቷቸዋል፤ ከዚህ የተነሳ መንፈሳቸው በፈጣሪና በሰዎች መካከል ሆኖ ዘወትር ይማልዳል ተብሎ በመታመኑ ነው።

የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ትንተና በሸካቾ ብሔረሰብ በሚል የጥናት ርዕሰ ጉዳይን ይዞ ወደ መስክ ስራ ከመሰማራት በፊትም ሆነ በጥናቱ ሂደት ከዚህ የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚቀራረቡና በብሔረሰቡ ባህልና ታሪክ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ድርሳናትን ለመዳሰስ ተሞክሯል፤ በዚሁ መሰረት ብሔረሰቡ ላይ ከተጻፉ ዘለግ ያሉ ታሪካዊ ጽሁፎች እንጀምር፤ አምባሳደር አበራ በጭሮ በ2014 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ታሪካና የባህል እሴቶች"፣ ወንድም ስሻ አንገሎ በ2013 "እናርያን ፍለጋ"፣ Lange በ1982 G.C "History of the thouthern Gonga" በሚል ያሳተሟቸው መጽሀፍት በታሪክ ዘውግ የሚመደቡ በመሆናቸው አንድ ላይ ያነሷቸውን ጭብጦች እንመልከት፤ ሸካቾዎች በታሪክ ሂደት ያሳለፋቸውን ውጣ ውረዶች፣ ኬት መጣነት፣ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር የነበራቸውን መስተጋብራዊ ግንኙነት፣ ልማዳዊ አስተዳደሮች፣ ማህበረ ፖለቲካዊ መዋቅሮች ሶስቱም መጻህፍት አንስትዋል። እነዚህ መጻህፍት የሸካቾን ታሪክ በስፋት ያቀረቡ ቢሆንም ስለ ሀገረሰባዊ የእምነት ሥርዓተ ክዋኔዎች አንስተው የተነተኑበት ሁኔታ አልታየም። በእርግጥ፤ ወንድምስሻ እናርየን ፍለጋ በሚለው መጽሃፋቸው 'ሀይማኖት ነክ ጉዳዮችን' (2013: 52-64) ባተቱበት ምዕራፋቸው የብሔረሰቡን መደበኛ ሃይማኖቶች በስፋት ሲመለከቱ የሸካቾ ብሔረሰብ ትውፊተዊ እምነቶች እንዳሉትና የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች እነዚህን ትውፊታዊ ክዋኔዎች እንደሚከውኑ ጥቆማ ሰጥተዋል። "በቀጣይ ቢጠኑ መልካም ይመስለኛል" (2013: 62) የሚለው ጥቆማቸውም ለዚህ ጥናት አቅጣጫ አመላካች ተደርጎ ይወሰዳል።

በኢትዮጵያ ቋንቋ ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በብሄረሰቡ ባህል ላይ ትኩረት ያደረጉ ጥናቶች ደግሞ፤ ፍጹም ብርሃኑ በ 2006 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ"። ምህረት ካሳ በ 2002 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና የአመጋገብ ስርዓት"። ስለሺ አባተ በ 2002 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት"። አማረ ሞላ በ1999 ዓ.ም "የሸካቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና"። ላይ የተደረጉ ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በብሔረሰቡ ባህል ላይ መደረጋቸው ከዚህ ጥናት ጋር በቅርበት ያመሳስላቸውል። ይሁን እንጂ በአምልኮ ስፍራዎች ላይ የሚፈጸሙ እምነት ነክ ክዋኔዎችን ጉዳያቸው አድርገው አልዳሰሱም፤ አልተነተኑም። በጥቅሉ የዚህን ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በጥናታቸው አላመላከቱም።

ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ ደግሞ፤ አውግቸው ወርቅአገኘሁ በ1989 ዓ.ም "ትውፊትና ባህላዊ ክንዋኔዎች በሸካ ብሔር" በሚል ለትያትር ትምህርት ክፍል ያቀረቡት የመመረቂያ ጽሁፍ

ለዚህ ጥናት ከሌሎቹ በተሻለ ቀረብ ያለ ነው። አውግቸው ብሔረሰቡ ላይ ትኩረት አድርገው ማጥናታቸው ብቻ ሳይሆን በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከወኑ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ሲተነትኑ የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ ክዋኔ አሁንም ድረስ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ እንደሚከወን ጥቆማ ሰጥተዋል። ከጥቆማ ባሻገር ገለጻና ትንተና ስላልተካሄደበት ምልዑነት ይጎድለዋል። Zewdie Kassa Tessema, Zemede Asfaw and Sebsebe Demissew በ 2020 ዓ.ም "Ethno-ecological study of medicinal and wild edible plants in Sheka Zone"፣ Behailu Ayele በ 2016 ዓ.ም "Exploretion into Co-Cultural communication between Manjo and donjo in Sheka" እና Workaferahu Ameneshewa በ 2015 ዓ.ም "Spatio-Temporal Forest Cover Change Detection Using Remote Sensing and GIS Techniques: In the case of Masha Woreda, Sheka Zone, SNNPRS, Ethiopia" በሚል የቀረቡ ጥናቶች ደግሞ በከፊል በብሔረሰቡ ባህል ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው። የነዘውዴ ጥናት በሸካ ዞን ውስጥ የሚገኙ ሀገር በቀል እጽዋቶች እንዴት ለሀገረሰብ ህክምና እንደሚውሉ የሚተነትን ነው። የበሀይሉ ጥናት ደግሞ በመንጃ እና ዶንጆ ጎሳዎች መካከል ያለውን የተግበቦት ስርዓት የተነተነ ሲሆን የወርቃፈራሁ ጥናት ደግሞ በሸካቾ ብሔረሰብ ውስጥ ያለው የደን ሽፋንና ስርጭት ምን ያህል እንደሆነ በሳይንሳዊ ቀመር ያተተበት ነው። የወርቃፈረሁ ጥናት ከሌሎች መሰል ቅይጥ (Mixed) ጥናቶች ተለይቶ እንዲዳሰስ የተመረጠበት ምክንያት "በማሻ ወረዳ የደን ሽፋን በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኘው ባህላዊ የእምነት ክዋኔዎች በጎሳ መሪዎች አካባቢ ባሉ የጉዶ (Gudo) እና የደዶ (Dedoo) ደኖች ውስጥ አሁንም ድረስ መከወናቸው ነው" (2015፣ 77) የሚል የጥናት መደምደሚያ መስጠቱ ነው። ይሁንና ወርቃፈረሁ ምን አይነት ክዋኔዎች እንዴት እና በምን መልክ እንደሚከወኑ በጥናቱ አላመላከተም።

በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ትኩረታቸው፤ በሸካቾ ታሪኮች፣ ተረቶች፣ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት እና የአመጋገብ ስርዓቶች፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት፣ ሀገረሰበዊ ትውን ጥበባት፣ በጂአይኤስ እና በስነ ምህዳር አጠባበቅ ዙሪያ የተደረጉ ናቸው። እስካሁን በተደረገው የቤተመጻህፍትና የወመዘክር እንዲሁም የኢ-ላይብረሪ ፍተሻ "በሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነቶች ሥርዓተ ክዋኔ" ላይ ትኩረት ያደረገ ምርምር ማግኘት አልተቻለም። ከዚህ የተነሳ "የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ ትንተና በሸካቾ ብሔረሰብ" የሚለው ርዕሰ ጉዳይ መጠናቱ በመስኩ ያለውን ሰፊ የእውቀት ክፍተት በመሙላቱ ረገድ ከፍ ያለ ሚና ይጫወታል።

ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔን በተፈጥራዊ መቼቱ ላይ በመመስረት፣ የክዋኔ መር እና የትዕምርት ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶችን ማንጠሪያ በማድረግ በጥልቀት የመረመረ ነው። የክዋኔ መር ንደፈ ሀሳብ ከበራን ለማጥናት አመቺ ንድፈሃሳብ በመሆኑ በዘመናችን ተቀባይነት እያገኘ እንደመጣ Atkinson (2004:109) ይገልጻሉ። የክዋኔ መር ንድፈ ሃሳብ በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው፤ ድርጊቱን ማን ፈጸመው ፣ ምን ተፈፀመ ፣ ለምን ተፈፀመ ፣ ድርጊቱ ለማን ቀረበ፣ መቼና የት ተፈፀመ ፣ እንዴት ተፈፀመ በሚሉ ዋና ዋና የክዋኔ ገጽታዎች እና አላባዎች ላይ ነው Bauman (1975:299)። እነዚህ አላባውያን ፎክሎርን በአውድ ለማጥናት የሚያስችሉ ሲሆኑ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ ምንነት ገልጸው የሚያሳዩም ናቸው። ስለሆነም በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ እየተመሩ የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የተፈፀመበትን ጊዜና ቦታ ፣ የክዋኔውን ህገ ደንብ፣ የክዋኔውን ሥርዓተ ሂደት፣ የተሳታፊዎችን ሁኔታ፣ የከዋኞቹን የአከዋወን ስልት፣ ሥርዓተ ክዋኔውና ይመለከቱ የነበሩ ግለሰቦች ለክዋኔው የነበራቸውን ስሜት፣ የድርጊቱን ቅደም ተከተል፣ መተንተን አስችሏል። በክዋኔ ላይ የሚታዩ ቴክስቶች ተምሳሌታዊ ትርጉማቸውን ተረድቶ ለመተርጎም ደግሞ ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብን ከክዋኔ መር ንድፈ ሀሳብ ጋር አንድ ላይ በማጣመር ቀርቧል። ትዕምርት (Symbol) የሚለው ቃል “አንድ የሚታይ ነገር፤ ቴክስት፣ ድርጊት፣ ቁስ ወዘተ በማህበረሰብ አጠቃላይ ስምምነት መሰረት የሚወከልበት

ስርዓት ሲሆን ‘አጠቃላይ ስምምነት’ የሚለው ሀሳብ በአንድ የተወሰነ ባህላዊ አውድ ውስጥ ብቻ የሚታይ መሆኑን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ Turner (1967: 151) ይገልጻሉ። ትዕምርት አንድን ነገር ወክሎ የሚቆም፣ በአንድ በተወሰነ ባህል ውስጥ አጠቃላይ ግንዛቤ የተደረሰበት ውክልናዊ ሂደት እንደሆነ ከገለጻው መረዳት ይቻላል። Cooke እና Macy እምነታዊ ክዋኔና ትዕምርት ያላቸውን ጥምረት ሲገልጹ፤ "ትዕምርት የከበራዎች መሰረት ነው፤ ትዕምርት የሌለባቸው ስርዓተ ከበራዎች የሉም (2005:14)። በማለት ከእምነታዊ ክዋኔዎች ጋር ያላቸው ጥምረት ምን ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ ያስረዳሉ። ከዚህ መሰረታዊ የንድፈ ሃሳብ ሀቲት በመነሳት በሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ከበራ ወቅት የሚከወኑ ክዋኔዎች ያላቸው የክወና ቅደምተከተል፣ ከዋኞቹ የሚጠቀሟቸው ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ውክልና፣ ግለሰቦች ያላቸው ማህበራዊና ባህላዊ ውክልና፣ የሚቀርቡ ክወናዎች የሚፈጥሩት የእርስበርስ ተግባቦትና የሚያሳዩት መስተጋብር፣ ከክዋኔው ጋር ግንኙነት ያላቸው ቁሶች፣ ማምለኪያ ስፍራዎችና አጸዶች፣ በንድፈ ሐሳቡ መነሻነት ትርጉም ተሰጥቷቸዋል።

### *የጥናቱ ዓላማ*

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በሸካቾ ብሔረሰብ የሸንበተ ቆጮ ክዋኔን መተንተን ነው።

### *የጥናቱ ሥነ ዘዴዎች*

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ገላጭ (Qualitative Descriptive) ምርምር ነው። አይነታዊ ገላጭ ምርምር ተፈጥሯዊ የሆነ፤ በልዩ ልዩ ዘዴዎች ሰዎችን በጥናቱ ውስጥ የሚያሳትፍ፤ በአውድ ላይ የሚያተኩር እና የሚተነትን ነው (Marshal & Rossman, 2006:1) ። ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔን በቅደም ተከተል በስፋትና በጥልቀት ይተነትናል። በእምነታዊ ክዋኔዎቹ ውስጥ የሚቀርቡ ቴክስቶች ትዕምርታዊ ውክልናቸው ይተረጎማል። የሀገረሰባዊ እምነት ተከታዮች የእምነት ሥርዓቶቹን በመከወናቸው የሚያገኟቸውን ጥቅሞች ይገልጻል።

በዚህ ጥናት መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ዓላማ ተኮር ንሞና (Purposive Sampling) ነው። በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ወቅት ከጥናቱ አካላይ መምረጥ የሚኖርባቸውን የናሙና አባላት የሚወስኑት ተመራማው ራሱ፣ የምርምሩ እና የጥናቱ አካላይ ባህሪ ናቸው (ያለው: 2009)። ይህን ዘዴ በመጠቀም ለዚህ ጥናት ተስማሚ የሆኑ ሁለት የንሞና ስልቶች ተመርጠዋል። የመጀመሪያው ዓይነተኛ ንጥል ንሞና (typical-case sampling) ሲሆን ይህንን የንሞና ዓይነት በመጠቀም የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ከሌሎች የሸካቾ ቀበሌዎች በተሻለ ትውፊታዊነቱን ጠብቆ አሁን ድረስ እየተከወነ ያለው አቴሶ[3] ቀበሌ በመሆኑ፤ የአቴሶ ጎሳ መሪን ጨምሮ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ 3፣ ከሌሎች 7 ቀበሌዎች ደግሞ 7 በድምሩ 10 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። ከአቴሶ ቀበሌ ውጪ ካሉ 7 ቀበሌዎች ደግሞ 14 ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች በድምሩ 24 መረጃ አቀባዮች በንጥል ንሞና ዘዴ ተመርጠው ተሳታፊ ሆነዋል። ሁለተኛው ጠቋሚ ወይም ተያያዥ ንሞና (network or snowball sampling) ነው። ይህ ዘዴ መረጃ ሰጪዎች ለአጥኚው በሚሰጡት ጥቆማ መሰረት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ግለሰቦች የሚመረጡበት ነው። ይህን የንሞና ዓይነት በመጠቀም

[3] (ቃ.መ ዳንበራዎ አለሙ፣ አምበሳደር አበራ 10/08/14)

የሸንበተ ቆጮን ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ምልከታ ከተደረገ በኋላ ንጥል ንሞና ወቅት በቁልፍ መረጃ አቀባዮች ጠቋሚነት የተገኙ ሁለት ተጨማሪ መረጃ አቀባዮች የተመረጡት በዚህ የንሞና ዘዴ ነበር።

በመስክ የፎክሎር መረጃን ለመሰብሰብ ጠቃሚ መሆናቸው ተደጋግመው የሚጠቀሱት ዘዴዎች፤ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ሲሆኑ ሶስቱም ዘዴዎች በዚህ ጥናት ተግባራዊ ሆነዋል። ተሳትፋዊ ምልከታን በመጠቀም የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ በተፈጥሯዊ መቼቱ ላይ በመገኘት ተጠንቷል። ሁለተኛው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው። የቃለ መጠይቅ ዘዴዎችን አስመልክቶ (Fife፤ 2005: 96) የተገደበ፣ ያልተገደበ እና በከፊል ያልተገደበ ብለው ከሚጠሯቸው ሶስት የቃለ መጠይቅ ዘዴዎች መካከል ያልተገደበ ቃለ መጠይቅና የተገደበ ቃለ መጠይቅ ዘዴዎችን በማመጣጠንና በማሰባጠር በጥናቱ ተግባራዊ ተደርጓል። ቃለ መጠይቅ በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረገው ስለህብረተሰቡ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት፣ የመከወኛ አጋጣሚ ዳራዎቹንና የክዋኔ ሁነቶቹን ቀድሞ ለመረዳት፣ ክዋኔዎቹ እንዴት፣ ለምንና እና መቼ፣ በዚህ መልክ መከወን እንደተጀመሩ ለማወቅ፣ በክዋኔ ላይ የሚቀርቡ ቃላዊ ትረካዎችን መልሶ ለማዋቀር፣ በማህበሩ ውስጥ በሚኖሩ ልዩነቶች ሳቢያ የአከዋወን ስርዓቶቹ የሚለያዩ መሆን እና አለመሆናቸውን ለማስረገጥ፣ ክዋኔዎቹ በዚህ መልክ መከወናቸው ለማህበሩ ያስገኛል ተብሎ ስለሚታሰበው ፋይዳ፣ በክዋኔዎቹ ስለሚስተዋሉ ቁሳዊ ባህሎች እና የአካላዊ እንቅስቃሴዎችን ትርጉም ለማግኘት ነው። ለቃለ መጠይቁ የተመረጡ ሰዎች በአራት ጎራ ተመድበዋል፤ እነዚህም ክዋኔዎቹን የሚመሩ ከዋኞች፣ በክዋኔዎቹ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑ ታዳሚዎች፣ ባህሉን በሚገባ የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የባህል ባለሙያዎች ሲሆኑ፤ 7 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች እና 17 ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች በድምሩ 24 መረጃ አቀባዮች የቃለ መጠይቁ አካል ሆነዋል። ይህም ትክክለኛና ሚዛናዊ የሆነ መረጃን ለማግኘት አግዟል። በሶስተኛነት ጥቅም ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የቡድን ተኮር ውይይት ነው። ይህ ዘዴ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴ ተፈትሸው በቂ ማብራሪያ ያልተገኘላቸው የእምነት ክዋኔዎች ላይ የተመረጡ መረጃ አቀባዮች በቡድን ሆነው እየተያዩ መረጃ እንዲሰጡ የሚደረግበት ዘዴ ነው። ውይይቱ በአንድ ቡድን የተዋቀረ እና 8 ተወያዮች ያሉበት ነው። ከተዋጽኦ አንጻር፤ 2ቱ የጎሳና የሀገረሰባዊ እምነቱ መሪዎች፣ 3 ከዋኞች፣ 1 የባህል ባለሙያ፣ 2 በብሄረሰቡ ማህበራዊና ታሪካዊ ሁነት ዙሪያ ጥልቅ እውቀት ያላቸው የብሔረሰቡ ተወላጆች ናቸው። ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ከተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን ለመተንተን ደግሞ ጥናቱ ገላጭ (Descriptive) የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ተከትሏል።

**የመረጃ ትንተና**

***የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ትንተና በሸካቾ ብሔረሰብ***

የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የሸካቾ ብሔረሰብ በቤት ውስጥ ከሚያከብራቸው ሀገረሰባዊ እምነቶች መካከል የሚመደብ ሲሆን፣ በአመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ለአባታዊ ሙት አማልክት መስዋዕት በማቅረብ አባወራዎች የሚያከብሩት በዓል ነው። የመጀመሪያው ሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የመኸር ምርት ሲደርስ ከታህሳስ ወይም ከጥር ወራት በአንዱ እሁድ የሚከበር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የበልግ ምርት መድረስን ምክንያት በማድረግ ከትንሳኤ በኋላ ባሉት እሁዶች በአንዱ ይከበራል። የመጀመሪያው ሸንበተ ቆጮ ክዋኔ እሁድ ላይ ከዋለ ከገና በዓል ወይም ከጥምቀት ወይም ደግሞ ከአስተርዮ ማርያም ጋር ተያይዞ ሊከበር ይችላል። ሁለተኛው የሸንበተ ቆጮ በዓል ደግሞ ምርት ከደረሰ ከትንሳኤ በዓል ጋር ወይም ከዳግማዊ ትንሳኤ በዓል ጋር ወይም ደግሞ ከበዓለ ሃምሳ ጋር ተያይዞ ሊከበር ይችላል። ይህ በዓል የቤቱ አባወራ ብቻ የሚያከብረው ሲሆን የሚከበርበትን ቀን

የሚወስነውም ራሱ አባወራው ነው[4]። ስለሆነም ሁለተኛውን የሸንበተቆጮ[5] ክዋኔ በአተሶ ጎሳ መሪ አቴስታታ[6] ዳኬቶ ቤት ከ22 እስከ 24/08/2014 ዓ.ም በመገኘት ክዋኔውን ከቅድመ ዝግጅቱ እስከ ክዋኔው ማግስት ድረስ ተፈጥራዊ መቼቱ በመገኘት መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል።

### *የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት*

የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ዝግጅት በዓሉ ከመድረሱ ከአንድ ወር በፊት ቀደም ብሎ የሚጀመር ነው። ቀዳሚው ዝግጅት ራስን ከማንጻት የሚጀምር ሲሆን ይህም የሚሆነው ለክዋኔው ቀደም ብለው የሚዘጋጁ አስፈላጊ የመጠጥ እና የምግብ ዝግጅቶችን ለመስራት የግድ የመንጻት ሂደትን ቀደም ብሎ መፈጸም ስለሚገባ ነው። ለበዓሉ የሚሆን ጠላ እና ጠጅ ለማድረስ በትንሹ አንድ ወር ይጠይቃል። የቅድመ ዝግጅቱ ሂደት ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜን ስለሚወስድ የማዕድ ቤቱን ስራ የመንጻት ሂደትን የጨረሱ፣ በአባወራው ቤት ውስጥ ካሉ ሴቶች[7] መካከል አንዷ ልታስጀምር ትችላለች። ነገር ግን በወር አበባ መምጣት፣ አካል ከመድማት፣ ወይም ከኮሶ አለመሻር፣ አስከሬን ከወጣበት ቤት ከመግባት ወይም ንጽህናን የሚያጓድሉ መተላለፎች ቢያጋጥሙ የመንጻትን ህግ የጨረሰች ሌላኛዋ ሴት ተክታ ልትሰራ ትችላለች። ብዙ ጊዜ ግን በባህሉ የሚመከረው የማዕድ ቤቱን ስራ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሴት ልጃገረዶች እንዲሰሩ ነው። ምክንያቱም እነሱ ለአቅመ ሄዋን ስላልደረሱና የወር አበባ ስለማያዩ ነው። ይሁንና እነሱም ቢሆኑ ንጽህናን ከሚያጓድሉ ነገሮች ራሳቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል። አባወራውም እንዲሁ የመንጻት ሂደትን ሳያልፍ የአባታዊ ሙት አማልክትን መስዋዕት ማቅረብ አይችልም። በመቀጠል አንድ በአንድ ለክዋኔው ቅድመ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን እንመልከት።

### *የመንጻት ህግን መፈጸም*

የሸንበተ ቆጮ ክዋኔን ለመከወን የመንጻትን ህግ ፈጽሞ መገኘት ቀዳሚው ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ይወሰዳል። ይህንን በዓል ሁሉም የሀገረሰባዊ እምነቱ ተከታይ የሆኑ አባወራዎች የአባታዊ ሙት አማልክት መስዋዕት በማቅረብ የሚያከብሩት[8] ነው። ምንም እንኳን ክዋኔው የወንዶች ወይም የአባወራዎች ቢሆንም የማዕድ ቤቱን የቅድመ ዝግጅት ተግባራት የሚከውኑት ሴቶች ናቸው። የማዕድ ቤት ዝግጅት፤ ከመጀመሪያው ምርት የጤፍ ጠላ መጥመቅ፤ ከመጀመሪያ የማር ምርት ጠጅ እና ብርዝ ማዘጋጀት፤ ከመጀመሪያ የበቆሎ ወይም የገብስ ምርት ቦርዴ ማዘጋጀት ፣ በርበሬ እና ሌሎች ቅመማ ቅመሞችን ማዘጋጀት ናቸው። ሴቶች ይህንን ለማዘጋጀት ከአንድ ወር በፊት ቀደም ብለው የመንጻት ህግን ፈጽመው ማስጀመር ይጠበቅባቸዋል። የቅድመ ዝግጅት

---

[4] ቃ.መ. ዳንበራኖ አለሙ 26/08/14

[5] ሸካቾ የሸንበተ ቆጮ በዓልን በዓመት ሁለቴ ወይም አንዴ ያከብራል፡፡ አንድ ግዜ ማክበሩ የግድ ቢሆንም ሁለተኛው ግን በራሱ ፍላጎት ወይም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ባህሉ ግዴታ አይጥልበትም፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም ጊዜያት የሚከበሩት ሸንበተቆጮዎች ተመሳሳይ ስለሆኑ ነው (ቃ.መ ዘውዴ ግችላ 27/0814 ዓ.ም)፡፡

[6] አቴስታታ የማዕረግ ስም ነው፡፡ አቴስታታ የሚለው ቃል 'አቴሶ' እና 'ታቶ' ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ጥምር ቃል ሲሆን አቴሶ ማለት ከሸካቾ ብሄረሰብ መካከል አንዱ ጎሳ ነው፡፡ ታቶ የሚለው ቃል ደግሞ መሪ ወይም ንጉስ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ አቴስታታ የአቴሶ ጎሳ መሪ ማለት ነው፡፡

[7] የጎሳ መሪዎች በብሔረሰቡ ውስጥ ከአንድ በላይ ሚስቶች እንዲያገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ምክንያቱም አንድም የማስተዳደር አቅም ስላላቸው ሲሆን አንድም ደግሞ የጎሳ መሪው ዓመቱን በሙሉ በመንጻት ህጋት ውስጥ ያለፉ ሴቶች እንዲያገለግሉት ባህሉ ስለሚያዝ ነው፡፡ ቃ.መ. ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ 18/08/15 ዓ.ም

[8] የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ በሁሉም የሀገረሰብ እምነት ተከታዮች እና በከፊል የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ሲከወን በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ ግን አይከወንም(ቃ.መ ወልታታ ባህሩ ወ/ጊዮርጊስ 26/0814 ዓ.ም)፡፡

ስራዎችን ለማስጀመር ከወር አበባ በኋላ ዘጠኝ ቀናት መቆየት፣ ከኮሶ ከሻሩ ሰባት ቀናትን መሻገር፣ አስከሬን ከወጣበት ቤት ከገቡ ዘጠኝ ቀናትን መሻገር፣ ጥፍርን አለመቁረጥ፣ አለመድማት፣ ራስን ለአደጋ ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅ፤ ከእሾህ ፣ ከመጥረቢያ ራስን ለዘጠኝ ቀናት ማግለል። ከእነዚህ አንዱ ከጎደለ ምልው የሆነ መንጻት አይኖርም። ይህን ሂደት ያልተሻገሩ ሴቶች ለመንጻት በተዘጋጀላቸው ጎጆ ራሳቸውን አግልለው ይቀመጣሉ።

አባወራውም የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ከመድረሱ ዘጠኝ ቀናት በፊት ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብ ይኖርበታል።[9] ክዋኔው ዘጠኝ ያህል ቀናት ሲቀሩት እንጨት ከመፍለጥ፣ አደን ከመሄድ መቆጠብ ይኖርበታል፤ ምክንያቱም ሊደማ ስለሚችል ነው። ከኮሶ መሻር በኋላ ሰባት ቀናት መቆየት፤ አስከሬን ከወጣበት ቤት ዘጠኝ ቀናት መዝለቅ ይጠበቅበታል። ንጽህናውን እንዳያስተጓጉል ለበዓሉ አስፈላጊ የማብሰያ እንጨቶችን ከዘጠኝ ቀናት ቀድሞ ማዘጋጀት አለበት።

በመንጻት ሂደት ውስጥ ዘጠኝ እና ሰባት ቁጥሮች ተደጋግመው መምጣታቸው ለምን የሚለውን ጥያቄ ያስነሳሉ፤ ይህን አስመልክቶ በቡድን ውይይት ወቅት መረጃ አቀባዮች የሚከተለውን ብለዋል፤ ባህሉ ለመንጻት ዘጠኝ ቀናትን መጠበቅ ወይም መዝለቅን የሚደነግገው ከፍ ላሉ መተላለፎች ነው። ለምሳሌ ሴት ልጅ ከወር አበባ እስክትነጻ ድረስ ከሶስት እስከ ዘጠኝ ቀናት ይፈጅባታል፤ ሰው ሰውነቱ ደምቶ ቁስሉ ለመድረቅ ከሰባት እስከ ዘጠኝ ቀናት ሊወስድበት ይችላል። በእነዚህ ምክንያቶች ነው ዘጠኝ ቀናት የንጽህና ማረጋገጫ ሆኖ የተደነገገው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ዘጠኝ ቁጥር በሸካቾ ባህል ሙሉ በሙሉ የመንጻት፣ የቅድስና፣ የፍጽምና በፈጣሪ (በየሮቺ) የመሰማት ምልክት ስለሆነ ነው ተብሎ ይታመናል። በዘጠኝ ቀናት ሁሉ ነገር ንጹህና የተቀደሰ ይሆናል፤ ከመርገምም ያጸዳል ተብሎ ይታሰባል። ከዚህም በሻገር ዘጠኝ ቁጥር ከጾምና ከጸሎት መልስ ጋር ይገናኛል። ለምሳሌ በባህሉ ቀኖና መሰረት የጎሳ መሪዎች በጾም ጸሎት ወቅት ዘጠኝ ሰዓት ድረስ መዝለቅ ይጠበቅባቸዋል። አንድ የሸካቾ አባወራ ዘጠኝ ሰዓት ከጾመና በየሮቺ ፊት ከተንበረከከ ጸሎቱ ወዲያው ይሰማል ተብሎ በማሕበረሰቡ ዘንድ ይታመናል[10]። በመንጻት ሂደት ሰባት ቀናትን መቆየት ወይም መሻገር የሚጠይቁት በባህሉ ቀላል ለሆኑ መተላለፎች ወይም ደግሞ የመንጻት ህግን ከመተላለፍ በፊት ከተከለከሉ ነገሮች ለመራቅ የተደነገገ ነው[11]።

### *የግብዓት አቅርቦት ዝግጅት*

ለሸንበተ ቆጮ የመስዋዕት ሥርዓተ ክዋኔ ግብአት የሚሆኑ ቅድመ ዝግጅቶች ከአንድ ወር በፊት ይጀመራሉ። የበዓሉ ተሳታፊዎች የመንጻትን ሂደት ከተሸጋገሩ በኋላ ለሸንበተ ቆጮ ተብሎ አነስተኛ አሮ (ንጹህ) የሆነ የሰንበት ጎጆ (ሸንበተ ከሮ) ይሰራል። እዚህ ጎጆ አካባቢ የመንጻት ህግን የተላለፈ ማንኛውም ሰው አይደርስም።

[9]ባህሉ ምንም እንኳን በዓሉ ከመድረሱ ዘጠኝ ቀናት በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም እንደሌለበት የሚደነግግ ቢሆንም፡፡ በሴቶቹ የሚሰራው የማዕድቤት ስራ እንዳይስተጓጎል ከአንድ ወር ጀምሮ ራሱን ከባለቤቶቹ (ከሚስቶቹ) ሊለይ ይችላል (ቃ.መ ዘውዴ ግችላ 27/0814 ዓ.ም)፡፡

[10] ቃ.ም አበራ በጭሮ 25/08/2014

[11] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዳንበራኖ አለሙ፣ ታምሪ ኮቶ፣ ዘለቀ ሻጫቸው፣ አየለች ሽሪፎ፣አበበ አንገሎ 29/08/14

ጎጀው ሲሰራ እግረ መንገድም ለበዓሉ ምግብና መጠጥ የሚሆን እንጨት ይፈለጣል። ለመስዋዕት የሚሆን አውራ ዶሮ፣ ለእንግዶችና ለሴቶቹ ማዕድ የሚሆን አነስተኛ ጠቦት[12] ይዘጋጃል።

ከዶሮና ከፍየል እርድ ውጪ ለጠላ ፣ ለጠጅ፣ ለብርዝ እና ለቦርዴ የሚሆኑ ግብዓቶችም ይዘጋጃሉ። እነዚህ ግብዓቶች በጠቅላላ ከቤት የሚመረቱ እና እቤት ውስጥ ብቻ የሚዘጋጁ ናቸው። ለጠላ የሚሆነው ጌፍ፣ ለማባያ የሚሆነው እንሰት፣ ለጠጅ የሚሆነው ማር እና ለቦርዴ የሚሆነው ገብስና በቆሎ ከቤት የሚመረት ነው። የሚፈጨውም እቤት ባለ ወፍጮ እንጂ ከተማ ያለ ዘመናዊ ወፍጮ አይነካውም። ምክንያቱም ከውጪ የሚገዛ እና የሚዘጋጅ ከሆነ በመንጻት ሂደት ውስጥ ያላለፉ ሰዎች ስለሚነኩትና ንጹህ ስለማይሆን ነው። ይህ ደግሞ መቅሰፍትን ወደ ቤት እንዲገባ ያደርጋል። የአባት ሙት አማልክት መንፈስ ያዝናል ተብሎ ይታመናል። ለሱ መቅረብ ያለበት ንጹህ እና የሚሰራውም ሰው ንጹህ መሆን ይኖርበታል። ካለበለዚያ ተስቦ ወደ ቤት ይገባል፤ ሴት ወንዱ ጤና አይኖረውም፤ ምርቱ በረከት ይርቀዋል፤ የቤተሰብ ሰላም ይናጋል፤ ልጆች ወላጅን የማይታዘዙ ይሆናሉ። ምክንያቱም መስዋዕቱ ተዘጋጅቶ ቢቀርብም እንኳን ካለ ንጽህና ነውና የአባት ሙት አማልክት መንፈስ በመስዋዕቱ አይደሰትም፤ ይጠየፈዋል ተብሎ ይታመናል።[13]

***የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ በዕለተ ቀኑ***

ከላይ በ 4.1. ለመጠቆም እንደተሞከረው የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ሥርዓተ ክዋኔ በሽካቾ አባወራዎች የሚከወነው ከምርት መድረስ ጋር ተያይዞ ባሉ ወራቶች ውስጥ ነው። የክረምቱ ምርት በታህሳስ ወይም በጥር ወራት ሲደርስ እንዲሁም የበልግ ምርት በሚያዝያ ወይም በግንቦት ወራት ደርሶ ሲታጨድ በአንደኛው እሁድ ይከበራል። በዚሁ መሰረት የበልግ ምርት መድረስን ምክንያት በማድረግ ሁለተኛው የሸንበተ ቆጮ ሥርዓተ ክዋኔ በአተሶ ጎሳ መሪ አቴስታታ ዳኬቶ ቀዬ ሚያዝያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ተከብሯል[14]። ይህ ክዋኔ በዕለተ ቀኑ የተጀመረው ከጠዋቱ 2፡00 ላይ ነው። የተጠናቀቀው ደግሞ ከቀኑ 8፡00 ላይ ሲሆን ክዋኔው በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ከዚህ በታች ቀርቧል።

***የመስዋዕት ማቅረቢያ ዝግጅት***

የመስዋዕት ማቅረቢያ ዝግጅት፤ ከጠዋቱ 2፡00 አካባቢ ለመስዋዕት መሰዊያ የሚሆን ስፍራ ከሸንበተ ቆጮ ቤት ጎን ባለ ጓሮ አባወራው እና ወንድ ልጆቹ ማዘጋጀት ይጀምራሉ። መስዋዕቱ የሚቀመጥበት የማርያም ባላ (ኤቀ በሎ) የተባለ እንጨት ከአባወራው ግቢ ባለ አነስተኛ ደን ውስጥ ይቆረጣል። አነስ ያለ በመብቀል ሂደት ላይ ያለ የዶቅማ ዛፍ ከነ ቅጠሉ ከዛው ደን ተቆርጦ ይመጣል። ቄጠማ (ጮጦ) ወይም ዘርጭ በአካባቢው ካለ ጨፌ በብዛት ታጭዶ ይመጣል። የቀረበው የመስዋዕት ማቅረቢያ መስሪያ ቁስ ከጓሮ ባለ እና ከተተከለ ብዙ ጊዜ ባስቆጠረ እንሰት አጠገብ መስራት ይጀመራል። ዶቅማው እና ኤቀ በሎው ከእንሰቱ ጋር ተደጋግፈው

---

[12] በአባወራው ቤት ብዙ ቤተሰብ ካለ ጠቦት ብቻም ሳይሆን እስከ ኮርማ ድረስ ሊታረድ ይችላል (ቃ.መ ዘውዴ ግችላ 27/0814 ዓ.ም)፡፡

[13] (ቃ.መ ዳንበራኖ አለሙ 29/08/14)

[14] በዚሁ ቀን የሸንበተ ቆጮ ሥርዓተ ክዋኔ፤ አምባሳደር አበራ በጭሮ፣ አቶ አበበ አንገሎ፣ ጎግራሻ መጅቶ፣ አቶ ቆመ ቆጭቶ ቤት ተከብሯል፡፡ ይህንንም ከ 27-29/08/2014 ዓ.ም ከግለሰቦቹ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲቆሙ ይደረጋል። ባላው ላይ እርጥብ ቄጠማ ይጎዘጎዛል። ከእንሰቱ እና ከዶቅማው ጎን ጦር ይቆማል። የመስዋዕት ማቅረቢያው ዝግጅት በዚህ ሁኔታ ሲከወን መመልከት ተችሏል።

የመስዋዕት ማቅረቢያውን ለመስራት የማርያም ባላ የ (ኤቀ በሎ) እንጨት የተመረጠበት ምክንያት ዛፉ ሲበቅል ከእናቱ ላይ መንታ ሆኖ እንደባላ ስለሚበቅል ነው። ባላነቱ አንድም መስዋዕት አቅራቢውን አባወራ ይወክላል። ባላ በባህሪው ተሸካሚና ደጋፊ እንደመሆኑ መጠን፤ አባወራውም የቤተሰቡ አቃፊና ተሸካሚ መሆኑን ሲያጠይቅ ነው። አንድም ደግሞ ባላው የመስዋዕት መሸከሚያ እና ደጋፊ በመሆኑ የአባቴ ሙት አማልክት መንፈስ ሆይ ከምርቴ የመጀመሪያውን መስዋዕት ተሸክሜ አቅርቤያለሁና ተቀበለኝ፤ እንደማለት ነው። በማደግ ላይ ያለ የዶቅማ እርጥብ እንጨት ተመርጦ ከኤቀ በሎው ጋር ተጣምረው የመስዋዕት ማቅረቢያውን መስራታቸው፤ የአባት እና የወንድ ልጆችን ህብረት፤ አባት ለልጆቹ የሚያስተላለፈውን የአባት ሙት አማልክት መስዋዕት የማቅረብን ሥርዓት ይወክላል። የዶቅማው ትንሽነትና ለጋነት የአባወራውን ወንድ ልጆች የሚወክል በመሆኑ አባወራው እኔና ወንድ ልጆቼ ያቀረብነውን መስዋዕት ተቀበልልን ሲል ነው። ኤቀ በሎው እና ዶቅማው እንሰቱን ተጠግተው መሰራታቸው በአባት ሙት አማልክት መንፈስ ጥላ ስር መኖራቸውን ለማጠየቅ ነው። ምክንያቱም አባወራው ግቢ ውስጥ ያለው በዕድሜ ትልቁ የእንሰት ተክል የአባት ሙት አማልክት መንፈስን ስለሚወክል ነው። ቄጠማ በባህሉ የደህንነት፣ የሃብት፣ የልምላሜ እና የመልካም ገጸበረከት ስጦታ ተምሳሌት ነው። የመስዋዕት ማቅረቢያው ላይ መጎዝጎዙም አንድም እኔ መስዋዕቴን በፍጹም ፍላጎትና ፍቅር ላንተ ለአባቴ ሙት አማልክት እንዳቀረብሁ፤ አንተም ደህንነቴን አረጋግጠህ የሚያስፈልገኝን ሀብትና በረከት ስጠኝ ብሎ መለማመንን ያጠይቃል። ጦር በሸካ ባህል በዋናነት ስኬትን ከማግኘት እና ከክፉ ነገር መጠበቅን ይወክላል። በዚህ የመስዋዕት ማቅረቢያ ላይ ጦር ግልጋሎት ላይ የዋለውም መስዋዕቱን ከክፉ ነገር ለመታደግ ነው[15]።

### *የመስዋዕት አቅርቦት ክዋኔ*

የመስዋዕት አቅርቦት ሥርዓተ ክዋኔው ከጠዋቱ 4፡00 ላይ ይጀመራል። አባወራው አቴስታታ ዳኬቶ ወንዝ ሄደው ገላቸውን በግራዋ ታጥበው የዳግም መንጻት ህግን ይፈጽማሉ። ክዋኔው ላይ ለመታደም የአባወራው ቤተሰቦች እና አራት ያህል የቅርብ ጎረቤቶች ወደ አባወራው ግቢ ይመጣሉ። አባወራው አቴስታታ ዳኬቶ ወደ ሸንበተ ቆጮ ጎጆ ገብተው የአምስት ደቂቃ ያህል ጸሎት አድርገውና ከጎጇቸው ፊት ለፊት ወንበር ወጥቶላቸው ይቀመጣሉ። በመቀጠል አገልጋያቸው የመስዋዕት ዶሮውን እና የመሰዊያ ቢላውን ይዞ ይመጣል። አባወራው ዶሮውን ከመሰዋታቸው በፊት የአባት ሙት አማልክታቸውን መንፈስ የሚለማመን ጸሎት ያደርጋሉ።

የአባታችን ካዊኖ መንፈስ ይህን መስዋዕት ተቀበል። በሰላም ወጥተን በሰላም እንድንገባ እርዳን ፤ ጤናችንን ጠብቅልን፤ ለምርታችን ረድኤትን ስጥልን። ለሴቶቻችን ልጆችን ስጥልን፤ የወለዱት ይደግላቸው፤ ልጆች የተባረኩና የቤተሰቦቻቸውን ትዕዛዝ እንዲሰሙ አድርግልን። ለቤተሰቦቼ ሰላም እና ጤና አድልልኝ፤ እኔም ይህንን መስዋዕት አቅርቤያለሁና እንዳልሰናከል አንተ ደህንነቴን ጠብቅልኝ።

ብለው ዶሮውን ሰውተው ደሙን የተዘጋጀው መሰዊያ ስር ያፈሳሉ (ምልከታ 23/08/14)። ደሙን አፍስሰው እንደጨረሱ የዶሮውን ቀኝ እግር ከታፋው ጀምረው በመገንጠል ለይተው ያስቀምጣሉ። ወንድ አንጋፋ ልጃቸው ደግሞ መሰዊያው አካባቢ እንጨት እና እንጨትን አፋጭተው እሳት ያቀጣጥላሉ።

---

[15] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዘለቀ ሻጫቸው ኦጎ ንገራሻ፣አየለች ሽሪፎ፣ አርቲስት ታምሩ ኩቶ፣ ተካልኝ ባራደራሻ 29/08/14 ዓ.ም) የአገላለጽ አጽንኦቱ የራሴ ነው፡፡

**ፎቶ 1፤ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መስዋዕት ሲቀርብ**



**ፎቶ በአጥኚው ፣ 23/08/2014 ዓ.ም በአቴስታታ ዳኬቶ ግቢ**

አባወራው ከቀኙ የዶሮ እግር ውጪ ያለውን የዶሮ ብልቶች ወንድ ልጆቻቸው ቤት ውስጥ ሰርተው ለምሳ እንዲያዘጋጁ ያዟቸዋል። አባወራው የቀኝ የዶሮ ታፋውን ቆዳ ለብቻ አውጥተው የራሳቸውን እና የወንድ ልጆቻቸውን እንዲሁም በከበራው ላይ የተሳተፉትን ወንዶች የቀኝ እግሮቻቸውን ጣቶች በቆዳው ይጠርጉላቸዋል። ይህን ክዋኔ እንደጨረሱ እጃቸውን በግራዋና በውሃ ታጥበው ወንበር ላይ ይቀመጣሉ።

በመቀጠል የአባወራው የቅርብ አገልጋይ (Qabechoo[16]) አባወራው የለዩትን ቀኝ ታፋ ይወስዳል። ከቤት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀ በርበሬ እና ቅመማ ቅመሞች በታናሽ ልጃቸው አማካኝነት ይመጣል። አገልጋዩ የቀረበለትን በርበሬ እና ቅመማ ቅመም ተጠቅሞ የታረደውን ዶሮ ቀኝ ታፋ በደንብ አድርጎ ያሸዋል። አሽቶ ከጨረሰ በኋላ በደንብ አድርጎ መጥበስ ይጀምራል።

ታፋው በደንብ ቃ ብሎ ከተጠበሰ በኋላ የመስዋዕት ማቅረቢያው ላይ ያኖረዋል። አብሮም በእንሰት ቅጠል በተሰራች አነስተኛ ዕቃ ለዚሁ ዓላማ አስቀድሞ የተዘጋጀ ቦርዴ በእንሰት በተሰራ ማቅረቢያ፣ ከቆጮ የተሰራ ህብስት (Shatee Kocoo) በእንሰት ኮባ (Mate Wamo) ተጠቅልሎ የመስዋዕት ማቅረቢያው (Eqa Beloo) ላይ ይቀመጣል።

---

[16] 'ቃበቾ' ያላቸው ሰዎች ብሔረሰቡን በጎሳ መሪነት የሚያገለግሉት ብቻ ናቸው፡፡

**ፎቶ 2፤ ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መባ የሚውል የቀኝ ታፋ ብልት የመጥበስ ክዋኔ**

**ፎቶ በአጥኚው፤ 23/08/2014 ዓ.ም በአቴስታታ ዳኬቶ ግቢ**

አባወራው መስዋዕት ከማቅረባቸው በፊት ወደ ወንዝ ሄደው በግራዋ መታጠባቸው የመንጻትን ህግ መጠበቃቸውን ማረጋገጫ ምልክት ነው። ውሃ ንጽህናን ይወክላል፤ ግራዋ ደግሞ ሰውነትን ከማንኛውም ነገር ያነጻል ተብሎ ይታመናል። ዶሮውን ሰውተው ቀኝ እግሩን ከነታፋው ገንጥለው ለመስዋዕቱ መውሰዳቸው ቀኝ በሸካቾ ባህል የደህንነት ምሳሌ ስለሆነ ነው። ይህን በዓልም የሸካቾ አባወራዎች የሚያከብሩት የአባታቸው ሙት አማልክት መንፈስ ሁሌ በቀኝ እንዲያውላቸው፣ በሰላም ወጥተው በሰላም እንድዲገቡ ነው። አባወራው ሁሌ ሸንበተ ቆጮን ባከበረ ሰዓት ከአፉ የማይለየው ጸሎት፤ "ለእኔና ለቤተሰቦቼ የደህንነት ዋስትና ሁነን የሚለው ነው" (ቃ.መ አቴስታታ ዳኬቶ፤ 24/08/14)።" የአባወራው አገልጋይ ቀኙን የዶሮ ታፋ ወስዶ በበርበሬ እና በቅመማ ቅመም ለውሶ እሳት ላይ መጥበሱ የአባት ሙት አማልክት መንፈስ መዓዛውን እንዲያሸት ጣዕሙን ደግሞ እንዲያጣጥም ነው። ከእንሰት የተሰራው ህብስት እና ከገብስ የተሰራው ቦርዴ በመስዋዕት ማቅረቢያው ላይ መቀመጡ፤ እኔ ከመጀመሪያ ምርቴ አስራት በኩራቱን ለአባቴ ሙት አማልክት ሰጥቻለሁና አንተም በምላሹ ቤቴን በበረከትና በረድኤት ሙላልኝ ሲል ነው።

አባወራው የዶሮውን የቀኝ እግር ቆዳ ወስደው የራሳቸውንና የወንዶቹን የቀኝ እግር ጣቶች ጠረግ ጠረግ ማድረጋቸው በባህሉ የወንድ አውራ ዶሮ ቆዳ ከማንኛውም ተናዳፊና ተናካሽ እንስሳቶች ይጠብቃል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቃ.መ ዳንበራኖ አለሙ 24/08/14)። ከዚህ በተጨማሪም በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፣ በሰላም አርሶና አድኖ ወደ ቤቱ እንዲመለስ፤ የደህንነት ማረጋገጫ ስለሆነ ነው። አንድ አባወራ ድንገት እግሩ ቢሰበር፣ ጤናው ቢጓደል፤ ህይወቱ አደጋ ላይ ቢወድቅ፤ ሸካቾ ያባትህን የሙት አማልክት መንፈስ

አላከበርክምን?' ብሎ ይጠይቀዋል። ካላከበረ ደግሞ ስርዓቱን በፍጥነት መከወንና መለማመን እንዳለበት ምክር ይሰጠዋል[17]።

**ፎቶ 3፤ ለአባት ሙት አማልክቱ የተሰራው መሰዊያና መስዋዕቱ**

**ፎቶ በአጥኚው 2014 ዓ.ም**

በአፍሪካ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ የእምነቱ ተከታዮች ክፋትን ለመቋቋም፣ ከክፉ ነገሮች ራሳቸውን ለማዳንና ለማንጻት መስዋዕት ማቅረባቸው የተለመደ ክዋኔ ሲሆን በመስዋዕት ውስጥ እንደ እንስሳና የአእዋፍ ደም ፣ ገንዘብ እና ሌሎች ስጦታዎችም በመስዋዕተነት ይቀርባሉ፤ የእምነቱ ተከታዮች መስዋዕት የሚያቀርቡት ከፈጣሪ፣ ከአማልክት ፣ ከቀድሞ የአባት ሙት አማልክት መናፍስት ወይም ደግሞ ከአካባቢ ጋር የጠፋና የተበላሸ ህብረትን ለመመለስ ሊሆን ይችላል በማለት (Adamo ፣ 1983) የገለጹት ሀሳብ ከሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ጋር መመሳሰሉን ልብ ይሏል። በ Adamo ገለጻ መሠረት በአፍሪካ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች መስዋዕቶች ይቀርባሉ። የመጀመሪያው፤ ከልዕለ ሃይላት፣ ከአማልክቱና መናፍስቱ ጋር እንዲሁም ከሰዎችና ከተፈጥሮ ጋር የተበላሸን ህብረት ለማስተካከል የሚቀርብ የመስዋዕት አይነት ነው። ሁለተኛው የመስዋዕት አይነት ደግሞ ማናቸውም አይነት ችግሮች በማህበረሰቡ ዘንድ አስቀድሞ እንዳይከሰቱ በማሰብ የሚቀርብ የመስዋዕት አይነት ነው።

ይህ የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የተከወነውም በአባወራው ቤተሰቦች ላይ ማናቸውም አይነት ችግሮች አስቀድሞ እንዳይከሰቱ በማሰብ መሆኑን ልብ ይሏል።

---

[17] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዳንበሬኖ አለሙ፡ ዘውዴ ግችላ፣ ዘለቀ ሻጫቸው፣ ኦጎ ንገራሻ፣ አየለች ሽሪፎ፣ አርቲስት ታምሩ ኮቶ 29/08/14 ዓ.ም)

### *ጸሎትና የአባት ሙት አማልክት ሚታዊ ተረክ ክዋኔ*

ጸሎትና የአባት ሙት አማልክት ሚታዊ ተረክ ሥርዓት ክዋኔ የመስዋዕት አቅርቦቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ይቀጥላል። ከቀኑ 6፡00 ላይ አባወራው ከመቀመጫቸው ተነስተው ወንድ ልጆቻቸውን እና ወንድ ተሳታፊዎችን ወደ ፊታቸው አስጠርተው ጸሎት ያደርጋሉ፤ "ያባቴ መንፈስ ሆይ አትጣለኝ። ቀሮ ላይ ወጥቼ በሰላም እንድወርድ፤ መንገድ ወጥቼ በሰላም እንድመለስ፤ ከቤትበሰላም ወጥተን በሰላም እንድንገባ፤ ልጆቼን ቤተሰቦቼን፣ መንደሬን ጠብቅ ፤ ለመጪው አመት ደግሞ እንዳከብርህ በህይወት አቆየኝ።" ብለው እንደጨረሱ ተሳታፊዎቹ "አሜን" በማለት ምላሽ ይሰጣሉ።

አባወራው ፤ "ይህንን የመስዋዕት በዓል የማቀርበው ለአባቴ ካዊኖ ሙት አማልክት መንፈስ ነው። ስለ ካዊኖ ትንሽ ላውራችሁ" ብለው ቀጠሉ፤

ከለታት አንድ ቀን ካዊኖ የሚባሉ ሰው ሸካ ውስጥ በሚገኝ ቶሮ በሚባል አንድ አካባቢ ተወለዱ። ከመወለዳቸው በፊት እርግዝናቸው አካባቢውን አነጋገረ። ምክንያቱም ባለቤታቸው አጠገባቸው አልነበሩም። ከለታት አንድ ቀን ባላቸው ለሊት ተኝተው አንድ ህልም ያያሉ። 'ወደ ቤትህ ስትሄድ ሚስቴ ያረገዘችው ከእኔ ነው ወይስ ከሌላ ነው ብለህ አትጠራጠር። ከእኔ በወጣ ቃል ነው ያረገዘችው።' ብሎ የሮቺ በህልም ለባለቤታቸው ተናገረ። ካዊኖም በድንግልና ካለ ወንድ ዘር ተረገዙ። ሲወለዱ በግራ ጎን ጥቁር በቀኝ በኩል ደግሞ ቀይ ሆነው ተወለዱ። ቅጽል ስማቸው ሞሆ ተባለ። ጨሌ መልክ ማለት ነው። ካደጉ በኋላ ብዙ አነጋጋሪ ተዓምራትን አደረጉ። ሲፈልጉ መታየት ሳይፈልጉ አለመታየት ቻሉ። አንዴ ቀይ አንዴ ጥቁር መሆን ቻሉ። የአዳሞቺ[18]ም መንፈስ ገባባቸው። አያቶቻችን እንደነገሩን ኡቃቢም በዚሁ ቶሮ በሚባል ስፍራ በካዊኖ ነው የተጀመረው። ካዊኖ በጣም ሃብታም ሆኑ። ብዙ ተዓምራቶችን በአካባቢው መስራት ጀመሩ። እሳቸው በየሄዱበት አካባቢ አጥር ሲያጥሩ ከብቶች እየመጡ ማደር ጀመሩ። በሃብት ላይ ሃብት አፈሩ። ከለታት አንድ ቀን ካዊኖ እንዲህ አሉ። 'እኔ የምሞተው ማክሰኞ ቀን ነው። በባህላዊ ልብስ አድርጋችሁ ቅበሩኝ። 40 ቀን ሲሞላ አፈር ቆፍራችሁ ተመልከቱኝ ፤ በግራ ጣቴ እንዶድ በቀኝ ትንሿ ጣቴ ደግሞ ዶቅማ በቅሎ ይገኛል። ይህንን ካያችሁ ምልክቴ ነው አሉ። በ40 ቀን እንዳሉት በግራ ትንሿ ጣት እንዶድ በቀኝ ደግሞ የዶቅማ ዛፍ በቅሎ ተገኘ። ከዚያ በኋላ ነው። አባቶቻችን ሸንበተቆጮን ማክበር የጀመሩት። አሁን እኔም በጸሎት ሳለሁ ካዊኖ በመንፈስ ተገልጠው አውርተውኛል፤ መሆን ያለበትን ነግረውኛል። እኔንም እናንተንም ባርከው ሄደዋል። ቀጣዩ ዘመንም ለሸካቾ ጥሩ እንደሆነ ነግረውኛል። ደስ ይበላችሁ። መስዋዕታችንና ጸሎታችን ተሰምቷል።

በማለት ተረካቸውንና ከካዊኖ የሰሙትን ትንቢታዊ አዋጅ ሲያጠናቅቁ ቤተሰቦቻቸውና ታዳሚው "አሜን" በማለት በደስታ ሲቀበሉ፤ ፍጹም የሆነ ደህንነትም ሲሰማቸው፤ የካዊኖ በመንፈስ ለአባወራው መገለጥና ምክር መስጠት ለታዳሚዎቹ ደስታ ሲፈጥር፤ ደጋግመውም አሜን...አሜን ...አሜን በማለት ምላሽ ሲሰጡ መመልከት ተችሏል።

[18] አዳሞቺ ፈጣሪ /የሮቺ/ ለሰው ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጠው መንፈስ ነው፡፡ የመንፈሱ ስያሜ ለሰው ልጆች አባት ከሆነው አዳም የተገኘ ነው፡፡ ቃ.መ ዳንበራኖ አለሙ 24/08/14

ካዊኖ[19] የአቴሶ ጎሳ የሙት አማልክት መንፈስ ናቸው። ፈጣሪ (የሮቺ) የአዳምን መንፈስ የሰጣቸውም እርሳቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል። እኒህ ሰው ከፊል ሰው ከፊል ደግሞ አማልክት ናቸው። ለዚህ ነው የሸካቾ ጎሳዎች ሽንበተ ቆጮን የሚያከብሩት፤ ካዊኖ ከሁሉ የአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ በላይ ናቸው። ምክንያቱም ሲጸነሱ ከሰውና ከመንፈስ በመሆኑ ነው። የመቅላታቸውና የመጥቆራቸው ሚስጥር የሰውና የመለኮታዊነት ባህሪያቸውን ለማጠየቅ ነው። ራሳቸውን የመግለጽና የመሰወራቸውም ሁነት ይሄው ከሰውና ከመለኮታዊነት ባህሪያቸው የሚመነጭ ነው[20]።

የሸካቾ ብሔረሰብ የሽንበተ ቆጮ ሥርዓት ክዋኔን የሚከውኑት የካዊኖን መንፈስ ለመለማመን ነው። ወንዶች ለአቅመ አዳም ደርሰው ትዳር ሲመሰርቱ የካዊኖን የአባት ሙት አማልክት መንፈስ ያከብራሉ። በማክብራቸው ጤናቸው ይጠበቃል፤ ሰላማቸው ይበዛል፤ እህል ገንዘቡ ረድኤት ይወርድበታል፤ በደህንነት ይመላለሳሉ ተብሎም ይታመናል።

አንድ የሸካቾ ብሔረሰብ አባወራ የሽንበተ ቆጮን ክዋኔ ለመከወን እምነቱ ከሚከለክላቸው ነገሮች ርቆ፤ በቅድስና እና በንጽህና ማክበር ከቻለ በሰራው የቅድስና ስራ ከሞት በኋላ ህይወት ያገኛል፤ እንደ ካዊኖ በገነት ተቀምጦ ስለ ቤተሰቦቹ ይማልዳል፤ ቤተሰቦቹን ይመክራል፤ ይገስጻል ተብሎ ይታመናል[21]።

***ማዕድ የመቋደስ ክዋኔ***

ማዕድ የመቋደስ ሥርዓተ ክዋኔ ከቀኑ 7፡00 ላይ የተዘጋጀው ማዕድ ይቀርባል። ወንዶቹ ለብቻ፣ አባወራው ከልጆቹ ጋር ለብቻ ይቀመጣሉ። ሴቶቹም ከቤት ውስጥ ለብቻ ይቀመጣሉ። ከመስዋዕቱ የተረፈው ቀሪው የዶሮ ብልት ተጠባብሶ ለአባትና ለወንድ ልጆቹ በትሪ ይቀርባል። ሴቶች እና ሌሎች ታዳሚዎች ግን ዶሮን አይመገቡም። በሸካቾ ብሔረሰብ ባህል መሰረት ሴቶች ዶሮ አይበሉም። ምክንያቱም ዱሮ ዱሮ ነው አሉ፤ ሴቶች እርስ በርስ በጣም ይዋደዱ ነበር። ከዚህ የተነሳ ባሎቻቸው ወደ ስራ ሲያቀኑ ዶሮን እንደ ቆጮ ጠቅልለው እያበሰሉ በየቀኑ መብላት ይጀምራሉ። ከራሳቸውም አልፈው ባላቸው በሌለበት ለውሽሞቻቸውም ያበሉ ነበር። ባሎች ስራ ውለው ማታ ቤት ሲገቡ ዶሮዎቹ የት ሄዱ ብለው መጠየቅ ይጀምራሉ። ሴቶቹም ዶሮዎቹን አውሬ እንደበላቸው አስመስለው ላባቸውን በመበታተን ለባሎቻቸው ያሳያሉ። ይህ ድግግሞሽ ሲበዛ ወንዶች መጠርጠር ይጀምራሉ። በሂደትም ሴቶቹ ራሳቸው አብስለው እየበሉ መሆኑን ይደርሱበታል። ከዕለታት አንድ ቀን ወንዶች ተሰባስበው የሸካቾ ብሔረሰብ ንጉስ ጋር ሄዱና እንዲህ ይሏቸዋል። "የመስዋዕት አቅርቦታችንን የአባታዊ ሙት አማልክት አልቀበል ያለው ሴቶች ዶሮ እየበሉ ስላስቸገሩ ነው።" ብለው ክስ ያቀርባሉ። ንጉሱም "የወንዶችን መስዋዕት የአማልክቱ መንፈስ እንዲቀበል ሴቶች ከእንግዲህ በኋላ ዶሮ እንዳይበሉ" ብለው አዋጅ ያስነግራሉ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ዶሮ አይበሉም።[22]

ለሌሎች ተሳታፊዎች የፍየል ስጋ ተጠብሶ ይቀርባል። የሚጠጣ ለሁሉም እንደየፍላጎቱ ቦርዴ፣ ጠላ፣ ጠጅ እና ብርዝ ይቀዳል። አባወራው ቁጭ ካሉበት በመነሳት "የሮቺ ሆይ ይህን ማዕድ ባርክልን" ብለው፤ የክዋኔው

---

[19] የአቴሶ ጎሳ የሙት አማልክት መንፈስ መጠሪያ ስም ነው፡፡

[20] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዳንበራኖ አለሙ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዘለቀ ሻጫቸው፣ አጎ ንገራሻ፣ አየለች ሽሪፎ፣ አርቲስት ታምሩ ኮቶ 29/08/14 ዓ.ም፡፡ የአገላለጽ አጽንኦቱ የአጥኚው ነው፡፡

[21] *ቃ.መ* ዳንበራኖ አለሙ ሸኖ 09/09/2014 ዓ.ም

[22] (*ቃ.መ* አቴስታታ ዳኬቶ 25/08/14)

*ታዳሚዎች ማዕዱን እንዲቋደስ ያዛሉ። እሳቸውም መጀመሪያ ከተቀዳው ጠላ ቀምሰው ለልጆቻቸው ያቀምሷቸዋል። ጓዳ ሴቶች የተጠባበሰላቸውን የፍየል ጥብስ ይበላሉ፤ የተቀዳላቸውን መጠጥ ይጠጣሉ። ሴቶችን የሚያስተናግዱት ሴቶች ሲሆኑ ወንዶችን ደግሞ ወንዶች ናቸው።*

የሚበላው ተበልቶ የሚጠጣውም ተጠጥቶ 7፡30 ላይ ማዕድ የመቋደሱ ሥርዓተ ክዋኔ ይጠናቀቃል።

ከላይ ለመግለጥ እንደተሞከረው አባወራውና ወንድ ልጆቹ ለሸንበተ ቆጮ የሚሆነውን መስዋዕትና ለማዕድ የሚሆነውን ዶሮ ሲያሰናዱ፤ ሴቶች ደግሞ ለራሳቸውና ለእንግዶች የፍየል ስጋ በወንዶቹ አስባርከው ይሰራሉ። በማዕድ ወቅት በቀኝ በኩል ያለው የዶሮ ክንፉም ሆነ እግሩ ለወንድምና ለወንድም ልጅ ወይም ለሌላ የቤተሰብ አባል ወይም ደግሞ ለሌላ እንግዳ አይሰጥም። ምክንያቱ ደግሞ ቀሪዎቹ የዶሮ ብልቶች ለመስዋዕቱ ከቀረበው የዶሮው የቀኝ እግር አካል በመሆናቸው በአባወራው እና በቤተሰቡ ላይ የሚመጣውን መልካም ነገር ወይም ጡር ይዘው ይሄዳሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው[23]።

### *የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ በበዓል ማግስት*

የሸንበተ ቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ክዋኔ ከበዓሉ ማግስት ጀምሮ ያሉት ጊዜያት ለአባወራውና ለቤተሰቡ የደስታ፤ የደህንነት እና የእረፍት ተደርጎ ይወሰዳል። አባወራው ንጽህናውን ጠብቆ እና ክዋኔያዊ ስርዓቱ የሚጠይቃቸውን ህግጋት አሟልቶ እንዲሁም ደግሞ ተሳክቶለት ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ መባውን በማቅረቡ ታላቅ ውስጣዊ እረፍት ያገኛል። ለአደን ባዶ ግሩን ጫካ ቢገባ እንኳን እሾህ አይወጋውም፤ እባብና ጊንጥ አይነድፈውም፤ አውሬ አይበላውም። ልጆቹን የትም ስፍራ ቢልካቸው ሃሳብ አይገባውም፤ ወጥተው ይሰናከላሉ ብሎ አይፈራም። ከሰው ጋር እጋጫለሁ ብሉ አይሰጋም። እታመማለሁ፣ ሰላሜን አጣለሁ ብሎም አይጨነቅም። ለራሱም ይሁን ለልጆቹ ህይወት አያስብም፤ ምክንያቱም ራሱንም ሆነ ልጆቹ በአባት ሙት አመልክት መንፈስ እንደሚጠበቁ እርግጠኛ ስለሆነ ነው[24]።

በማግስቱ አባወራ አቴስታታ ዳኬቶ ልጆቻቸው ደህንነት ተሰምቷቸው ወደ ስራ እንዲሰማሩ ያዟቸዋል። ሰኔ ከመድረሱ በፊትና ክረምት ከመግባቱ በፊት ማሳ ላይ ተሰብስቦ ያላለቀ ምርት ካለ ተሰብስቦና ተወቅቶ ወደ ጎተራ እንዲከማች፤ በጫካ ያለው ማር ተቆርጦ ቤት መግባት ያለበት ፣ መሸጥ ያለበት መሸጥ እንዳለበት ይነግሯቸዋል። ከሰኔ በኋላም ማሳው ለክረምቱ ዝግጁ እንዲሆን፣ በርከት ያሉ የንብ ቀፎዎች ከወዲሁ እንዲዘጋጁም ያሳስቧቸዋል። የአባወራውን ትዕዛዝም ልጆቻቸው በደስታ ይቀበላሉ።

የአባወራው ልጆች ደስታ አንድም የአበታዊ ሙት አማልክት መንፈስ በመዘከሩ በቤተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን መቅስፍት ማስቀረት በመቻሉ አንድም ደግሞ ቀጣዩ ዓመት የስኬትና የበረከት ይሆናል የሚል ጽኑ እምነት ስላላቸው ነው። አባወራው ባይሳካለትና ለአባታዊ ሙት አማልክ መንፈስ መስዋዕት ባያቀርብ ከአባወራው ይልቅ ልጆቾ በስጋት ይወጠራሉ፤ በሰላም ወጥተው በሰላም ስለመግባታቸው እርግጠኛ አይሆኑም። ለዚህ ነው ልጆቹ የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ መከወኑ ያስደሰታቸው።

## *ማጠቃለያ*

---

[23] *ቃ.መ* አቴስታታ ዳኬቶ፣ 26/08/14 ዓ.ም)

[24] ቡ.ው አቴስታታ ዳኬቶ፣ ዘውዴ ግችላ፣ ዘለቀ ሻጫቸው 29/08/14 ዓ.ም

ይህ ጥናት የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ተፈጥሯዊ መቼትን በመጠቀም ከቅድመ ዝግጅቱ እስከ በዓሉ ማግስት ድረስ ያለውን የክዋኔ ሂደት በቅደም ተከተል ተንትኗል።

የሸንበተቆጮ ሀገረሰባዊ እምነት ለአባታዊ ሙት አማልክት መንፈስ የሚቀርብ የመስዋዕት ክዋኔ መሆኑን፣ ክዋኔው ላይ የተነገሩ ቴክስቶች፣ የቀረቡ ቁሶችና የተፈጸሙ ድርጊቶች ያላቸው ትዕምርት በጥናቱ ተፈክሯል።

የአባት ሙት አማልክት መንፈስ ከምድራውያን ቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የአባትና ልጅ መሆኑ፣ ወደ ምድራዊ ዘመዶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው በመንፈስ ሊቀርቡና ሊታዩ እንደሚችሉ እንዲሁም ከማይታየው ሰማያዊ ዓለም ሆነው ቤተሰቦቻቸውን ማማለድ ይችላሉ ተብሎ በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ እንደሚታመን ጥናቱ አመላክቷል።

ሸንበተ ቆጮን በንጽህና እና በቅድስና ሳያቋርጡ በመከወን፣ ከሞት በኋላ ባለው ህይወት የአባት ሙት አማልክት መንፈስ የመሆን ዕድልን ያጎናጽፋል ተብሎ እንደሚታመን ጥናቱ አሳይቷል።

በመጨረሻም ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ የሚከተሉት ፋይዳዎች አሉት።

ከተጠኝ ብሔረሰብ አንጻር፤ ከሰማይ አምላክና ከአባታዊ ሙት አማልክት እንዲሁም ከአካባቢ ጋር የጠፋና የተበላሸውን ህብረት ያስመልሳል፤ የአባት ሙት አማልክት ምክር በራስ የመተማመን ስሜት እንዲፈጠርባቸው፣ ምቾት እና ደህንነት እንዲሰማቸው ያደርጋቸልዋል፤ የአባት ሙት አማልክት መንፈስ በተለያዩ ጊዜያት ያስተላለፏቸው ህጎች፣ ደንቦች እና ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ባህላቸውንና እምነታቸውን እንዲጠብቁ አስችሏቸዋል፤

ለሀገር ከሚያበረክተው ፋይዳ አንጻር ፤ የሸንበተ ቆጮ ክዋኔ ለአካባቢ ሥነምህዳር መጠበቅ የራሱን ሚና ይጫወታል። ክዋኔውን ለመፈጸም የሚውሉ ግብዓቶች የሚገኙት ከአካባቢው ካሉ የደዶ እና ኮቦ ደኖች በመሆኑ አባወራው እነዚህ የደን ሃብቶችና በዙሪያው የሚገኙ የዕጽዋት አይነቶች እንዳይመናመኑ ይጠብቃቸዋል፤ በተጠቀሙት የእጽዋት አይነት ምትክ ችግኞችን ይተክላል፤ አባወራው መስዋዕቱን ለአባት ሙት አማልክት የሚያቀርበው ምርታማ ሲሆን በመሆኑ ዝናብ እንዳይቋረጥ፣ የአካባቢው ሥነ ምህዳር እንዳይጎሳቆል በዙሪያው ያሉ ደኖችን በኃላፊነት ስሜት ይጠብቃል።

## *ማጣቀሻዎች*

ምሕረት ካሳ። 2002 ዓ.ም)። "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የምግብ ዝግጅት እና አመጋገብ ስርዓት።" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ስለሺ አባተ።2002 ዓ.ም። "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት።" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አበራ በጭሮ። 2014 ዓ.ም። *የሸካቾ ብሄረሰብ ታሪክና የባህል እሴቶች።* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

አማረ ሞላ። 1999 ዓ.ም። "የሸካቾ ብሄረሰብ ሃገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና።" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አውግቸው ወርቅአገኘሁ።1989 ዓ.ም። "ትውፊትና ባህላዊ ክንዋኔዎች በሸካ ብሔር።" በትያትር ትምህርት ክፍል፣ ለ ቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ወንድምስሻ አንገሎ። 2013 ዓ.ም። *እናርያን ፍለጋ።* አዲስ አበባ፣ ብራና መፃህፍት መደብር።

ያለው እንዳወቀ። 2009 ዓ.ም። *የምርምር መሰረታዊ መርህዎችና አተገባበር።* አዲስ አበባ፣ ተፈራ ስዩም ፕሪንቲንግ ፕሬስ።

ፈቃደ አዘዘ። (1991 ዓ.ም)። *የስነቃል መምሪያ።* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

ፍጹም ብርሃኑ። (2006 ዓ.ም)። "የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ።" በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሙያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

Adamo, D. 1983. "The Church in Africa and African Traditional Religious Beliefs and Practices". Rel. D. dissertation, Indiana Christian University.

Atkinson, P. 2004. Review Essay. *British Journal of Sociology of Education,* 25(1): 107-114.

Behailu Gebrehiwot. 1953. "Omens in Ethiopia". In Alula Pakhurst (ed.). *Ethnological Society Bulletin*, Vol 1, no1-10 and Vol II no. 1. Addis Ababa University.

Bell, C. (1997). *Ritual Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University Press.

Bauman, R. 1975. "Verbal Art as Performance". *American Anthropologist, New Series* (77).2,290-311.

Cooke, B. and Macy, G. 2005. *Christian Symbol and Ritual. An Introduction*. New York: Oxford University Press.

Goldstein, K. (1964). *Guide for Field Workers in Folklore*. London: Associates, Inc.

Marshal, M & Rossman, G. 2006. *Designing Qualitative Research*. 4th Ed. United States of America: Saga Publication Inc.

Mbiti, J.S. (1970). *Concepts of God in Africa*, SPCK, London.

Oborji, F.A. (2002). *"In Dialogue with African Traditional Religion*". *New Horizon, Mission Studies*. 19 (1: 13-34.

Sims, M. C, and Stephens, M. 2005. *Living Folklore: An Introduction to the Study*. Utah State University Press.

Steup, M. 2001. *Knowledge, Truth, and Duty*: Essays on Epistemic Justification, Responsibility, and Virtue. ED. Oxford University Press.

Turner, V. 1967. *The Forest of Symbols: Aspects of Ndembu Ritual*. Ithaca, New York: Cornell University Press.

Fife, W. 2005. *Doing Fieldwork:* Ethnographic Methods for Research in Developing Countries and Beyond. England: Palgrave Macmillan

Workaferahu Ameneshewa 2015. "Spatio-Temporal Forest Cover Change Detection Using Remote Sensing and GIS Techniques: In the case of Masha Woreda, Sheka Zone, SNNPRS, Ethiopia". Addis Ababa University

Lange, W. J. (1982). History of the Southern Gonga (southwestern Ethiopia). Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.

Zewdie Kassa, Zemede and Sebsebe 2020. "Ethno-ecological study of medicinal and wild edible plants in Sheka Zone". *Tropical Plant Research* 7(1):65-75